# **የፍትሕ ቤቶች ዌብናር፣ ቪድዮ ቅርፅ ትርጉም**

**ስላይድ 1**

በኮሎምብያ ዲስትሪክት የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በተዘጋጀው ***የእኩል እና ሁሉንም የሚያካትት ትክክለኛ የፍትሕ ቤቶች ዕቅድ፣ ለተጠቃሚዎች ዕውቀት*** ዌብናር ዝግጅት እንኳን ደህና መጣችሁ። ስሜ ________________

እና ________________________ በ__________________።

የቤቶች አድልዎ በሀያኛው ክፍለ ዘመን እና ከዛም ቢፊት ባሉት ጊዜያቶች በእኩልነት እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ ቦታ የያዘ ክፍል ነው። ካለፉት ጥቂት ምልዐተ ዓመታት ጀምሮ ስለ እኩልና ሁሉን ያካተተ የቤት ገደቦች ጉዳይ ስናስብ በአእምሮችን የሚመጡት እንደ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ያሉ ታዋቂ ሰዎች ናቸው። የ1968 ዓ.ም. ፍትሕ የቤቶች ድንጋጌ በሥራ ላይ መዋልና መሻሻል እና በመላው በሀገሪቱ ውስጥ ፍትሕ የቤቶች ድልድልን ለማስፋፋት በተደረገው ቃል ኪዳን ከፍ ያለ መሻሻል አድርገናል። ምንም እንኳን እነዚህ ሙከራዎች ቢደረጉም ቤትን የተመለከተ አድልዎ ለተወሰነ ክፍል አሁንም አሳሳቢ ጉዳይ ነው። የት እንደምንኖር የምናደርገው ምርጫ በሥራችንና የትምህርት ዕድል፣ በቤተሰብ አካባቢ መኖርን፣ መጓጓዣ የማግኘትን፣ የንግድና የመንግሥት አገልግሎቶችን የማግኘትና በራሳችንን ደህንነት መብቶች ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል።

ዛሬ ስለመጣችሁ ደስተኞች ነን። ምክንያቱም፣ የቤት አድሎ ጥረቶችን ከፍትህና ሰባዓዊ መብቶች ሥራዎቻችን ጋር አጣምረን መሥራቱ ጠቃሚ ነው። የዛሬው ዌቢናር ለምታደርጉት ሥራ እንደሚጠቅማችሁ ተስፋ እናደርጋለን። ስለ ቤቶች አድልዎ ጉዳይ በዲ.ሲ.. የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ ድህረ ገጽ — ohr.dc.gov — እና በፌስ ቡክ ገጽ facebook.com/dcohr ተመልከቱ።

**ስላይድ 2**

የዚህ ዌቢናር ዝግጅት ወጪ የተከፈለው በአሜሪካ የቤቶችና የከተማ ልማት (HUD) መሥሪያ ቤት ነው። የቤቶችና የከተማ ልማት (HUD) መሥሪያ ቤት ጠንካራ፣ ዘላቂ፣ ሁሉንም ሕብረተሰብ ያካተተ ተመራጭ እና በገቢ መጠን የሆኑ ቤቶችን ለማቅረብ ተስፋ ያደርጋል። ለሁሉ እኩል የሆነ ቤትን በተመለከተ የቤቶችና የከተማ ልማት (HUD) መሥሪያ ቤት ሁሉን ሕብረተሰብ ያካተተ ዘላቂ፣ አድሎ የሌለበት ቤቶች ለመገንባት ይጥራል። የሰባዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) በቤቶች ላይ ያለ አድሎን በተመለከተ ያሉ አቤቱታዎችንና በተመለከተ ከቤቶችና የከተማ ልማት (HUD) መሥሪያ ጋር በቅርብ ይሠራል።

**ስልይድ 3**

የሰባዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ዓላማ አድሎን ለማጥፋት፣ የእኩልነት መብትን ለመጨመር እና የኮሎምብያ ዲስትሪክትና የፌደራል አድሎ ያለማድረግ ሕጎችን በማስከበር የሰበዓዊ መብቶችን ለማስጠበቅ ነው። የሰባዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አድሎ ከመፈፀሙ በፊት ለማስቀም የጥብቅና ተግባር ቢሠራም፣ የዚህ የዲስትሪክቱ ኤጀንሲ መሠረታዊ ሥራው ............................................

**ስላይድ 4**

...በቤቶች፣ በሥራ፣ በሕዝብ መኖሪያዎች እና የትምህርት ተቋሞች አካባቢ ለቢሮው የተመለከቱ አድሎአዊ የሆኑ አቤቱታዎችን መመርመር ነው። ዛሬ የምንነጋገርበት የሚያተኩረው የቤቶችን አቤቱታ በተመለከተ ነው። የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) በሁለት ሕጎች ላይ ያተኩራል፦ የ1977 የዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እና የ1968 ፌደራል ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ እና ማሻሻያዎቹ ላይ ያተኩራል።

**ስላይድ 5**

ማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅቶች፣ የቡድን ቤቶች፣ የጥብቅና እና የፍትህ ቤቶች ቡድኖች እንዲሁም የማይንቀሳቀስ ንብረት ኤጀንቶች የሚከተሉት በደሎች እስከደረሱባቸው ድረስ የአድሎ አቤቱታ ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ማቅረብ ይችላሉ:

- ግለሰቡ እውነተኛ ወይም በማስፈራራት የአድሎ ጥቃት ከደረሰበት
- ተከሳሽ (ወይም ቤት አከራይ) በዲ.ሲ. ንግድ ካለው
- ጉዳዩ በዲ.ሲ የፍትሕ ቤቶች ድንጋጌ ወይም በዲ.ሲ. ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ከተሸፈነ
- አቤቱታው አድሎው በተደረገ በአንድ ዓመት ውስጥ ከቀረበ

**ስላይድ 6**

በሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በኩል አቤቱታ ማስገባት ጥቅሙ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ጠበቃ የማያስፈልገው ነፃ የአቤቱታ አገልግሎት ያገኛል። ይህም ከብዙ ማሕበራዊ ወይም የኢኮኖሚ ክፍል የታቀፉ ክፍሎችን የመደመጥ ዕድል ይሰጣቸዋል። አቤቱታ ለማስገባት.......

**ስላይድ 7**

...ግለሰቦች ቀላል የሆነ የአቤቱታ ቅጽ በኦንላይን በመሙላት ወይም ጁዲሽያሪ ስኩዌር ሜትሮ ማቆሚያ በሚገኘው የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ በመሄድ ማመልከት ይችላሉ። ቅጹን ከሞሉ በኋላ ስለቤት ጉዳይ አቤቱታው ለመርማሪ በቃለ መጠይቅ እንዲያስረዱ ወደ ቢሮ እንዲመጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

**ስላይድ 8**

ከማመልከቻ ቃለ መጠይቁ በኋላ፣ በአቤቱታው ላይ ሥልጣን እንዳለውና እንደሌለው ይወስናል። ሥልጣን ካለው የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ አቤቱታውን ተቀብሎ ጉዳዩ በፌደራል ሕግ የሚሸፈን ከሆነ ለአሜሪካ የቤቶችና ከተማ ልማት ቢሮ ይልከዋል።

ጉዳዩ ተቀባይነት ካገኘ ምርመራ ማካሄድ ይጀመራል። እንዲሁም አቤቱታ ባቅራቢውና በተከሳሹ ወይም አድሎውን በፈጠረው ሰው መካከል ስምምነት ለመፍጠር ይሞክራል። የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) በከሳሽና በተክከሳሽ መካከል ዕርቅ መደረግ ግዴታ ነው ብሎ በማመን የተለየ ድርጅት ነው። ሁለቱም ወገኖች ቤቱን የማግኘት ጉዳይ፣ የገንዘብ ጉዳይ፣ አስፈላጊ ሠራተኛ ማሰልጠንን ወይም ሌሎች መፍትሄዎችን በተመለከተ ከየሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አስታራቂ ጋር ተገናኝተው በስምምነት ለጉዳዩ መፍትሄ ለመስጠት ይሞክራሉ።

**ስላይድ 9**

*ሆኖም፣ ማስታረቁ ካልተሳካ ጉዳዩ ፍጻሜ እስከሚደርስ ድረስ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ምርመራውን ይቀጥላል። ምርመራው ከሳሹን፣ ተከሳሹንና ምስክሮቹን ማነጋገር፣ ሰነዶችንና ፖሊሲዎችን መመርመርና ሌሎች መንገዶችን ያካትታል። ምርመራው ካለቀ በኋላ...*

**ስላይድ 10**

*...የምርመራው ውጤት ለሰብዓዊ መብቶች ጠባቂ ዋና አማካሪ ውጤቱን መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለዲሬክተሩ እንዲያስተላልፍ ይላካል። የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) ዲሬክተር ውሳኔውን መርምሮ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል። በቂ ማስረጃ ከተገኘ ሁለቱም ወገኖች ለእርቅ እንደገና ተገናኝተው እንዲነጋገሩ ይሞከራል። ስምምነት ካልተደረሰ...*

**ስላይድ 11**

*...ጉዳዩ ለዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ይላካል። በዛም ከሶስቱ አንዱ የአስተዳደር ዳኛዎች የቀረበውን መረጃ መርምረው አድልዎ መድረሱን ወይም አለመድረሱን ይወስናሉ። በከንቲባው የተሾሙ ኮሚሽነሮቹ የዳኛውን ፍርድ መርምረው በውጤቱና በፍርዱ ሊስማሙ ወይም ሊሽሩት ወይም ሊላ ፍርድ ሊጠይቁ ይችላሉ። የመጨረሻውን ውሳኔ የሚያደርጉት ኮሚሽነሮቹ ናቸው።*

**ስላይድ 12**

*አሁን ከየሰብአዊ መብቶች ጠባቂ የአቤቱታዎች አሠራር ወደ የዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እንተላለፋለን።*

*የ1977 የዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ በሀገሩ ካሉት አድልዎ ያለማድረግ ሕጎች ግንባር ቀደም ቦታ ከያዙት ሕጎች አንዱ ነው። ቅድም እንደጠቀስኩት ድንጋጌው በቤት፣ በሥራ፣ በሕዝብ የመኖሪያ ቤቶችና በትምህርት ተቋሞች የሚፈፀሙትን አድልዎ ያግዳል።*

**ስላይድ 13**

*የዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌን ካሉት አድልዎ ያለማድረግ ሕጎች ግንባር ቀደም ቦታ ከያዙት ሕጎች አንዱ ነው የምንልበት ምክንያት የፌደራሉ የፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ለሰባት ቡድኖች ጥበቃን ሲሰጥ የዲ.ሲ. ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ለ18 የተጠበቁ ቡድኖች ጥበቃ ያደርጋል። በፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ውስጥ ያለተካተቱ የሚከተሉትን ይጨምራሉ፦ በሰውነት አመለካከት፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ልዩነት ወይም አባባል፣ የትምህርት ደረጃ እና የፖለቲካ አቋምን ያካትታል።*

**ስላይድ 14**

*ሌላው በዲ.ሲ. የቤቶች አድሎ የሌለበት ሕግ የተሸፈነ ግን በፌደራል ያልተካተተ ባሕሪይ በቤተሰብ ውስጥ የተፈጠረ ጥቃት ነው። ይህ የሚከለክለው:*

- የቤት ውስጥ ሁከት የደረሰበትን ሰው ፀጥታውን ወይም ደህንነቱን ለማሻሻል ጥረት አለማድረግ
- በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት የደረሰበትን ሰው የኪራይ ኮንትራቱን ያለጊዜው ያለቅጣት ለማቋረጥ አለመፍቀድ፣ ወይም
- ጥቃት የደረሰበትን ሰው ለአጣዳፊ እርዳታ ፖሊስ የመጥራት መብቱን መከልከል ወይም መወሰን

በቤተሰብ ውስጥ የተፈጠረ የጥቃት ሁኔታ በዲ.ሲ. የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተጨመረ ጠቃሚ የሆነ መብት ነው።

**ስላይድ 15**

ባጠቃላይ የፍትህ ቤቶች አካባቢን በተመለከተ የዲ.ሲ. ሕግ ከፌደራሉ ሕግ ይልቅ ሁሉን ያቀፈ ነው፣ 18 ቡድኖች በሕጉ ይጠበቃሉ። ይህም ማለት ተከራይ ሆኑ ወይም የቤት ባለቤት፣ ለብድር አመልካች ሆኑ ወይም አፓርትመንት ለመከራየት አመልካች ከሆኑ አድልዎ እንዳይደርስብዎት በ18 መለያዎች በህግ ይጠበቃሉ።

**ስላይድ 16**

አሁን ስለፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ጠለቅ ብለን እንመለከታለን፡

ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ዓላማው ለጥቂቶች ሳይሆን ለሁሉም በእኩልነት ቤት እንዲያገኙ መርዳት ነው። ስለፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ስንነጋገር፣ አመጣጡን ማወቅ አለብን፡ - ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ሕጋዊ ሲሆን ሰዎችን ማግለል ከቁጥጥር ውጭ ነበር። በብራውንና የትምህርት ቤቶች ቦርድ መካከል የነበረው ድርድር ያለፈው ከትንሽ ዓመታት በፊት ነበር። በዚያን ጊዜ ሰዎችን ማገለልን ለማስቀም በየስቴቱ የጂም ክሮው ሕግ ያስከብሩ ነበር።

**ስላይድ 17**

ድንጋጌው መጀመሪያ ሲያልፍ ያካተተው ዘር፣ ቀለም፣ ብሔርና ኃይማኖትን ነበር። ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ በኋላ በመሻሻል ፆታን እንደገና በማሻሻል የአካል ጉደተኝነትንና የቤተሰብ ሁኔታን አካተተ።

**ስላይድ 18**

ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ በጣም ሰፊ ያለ ነው። በማንኛውም የቤት ጉዳይ፣ ኪራይ ከመከልከል ጀምሮ እስከ ብድር አለመስጠት፣ አገልግሎቶችን መንፈግ ወይም መወሰን፣ በዘር፣ በብሔር ወይም በፆታ ልዩነት አድልዎ ማድረግ ይከለክላል።

**ስላይድ 19**

ሌላው አድሎ የተለዩ የሕብረተሰብ አካሎች ወደ አካባቢው እንዳይገቡ ማገድ ነው። ይህም የሚሆነው አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ኤጀንት የንብረቱን ባለቤት የተለዩ ሕብረተሰቦች ወደ አካባቢው እየገቡ ስለሆነ ንብረቱን እንዲሸጥ ሲገፋፋው ነው። ለምሳሌ፦ አካባቢው የሚኖሩት ነጮች ከሆኑ፣ ኤጀንቱ የንብረቱን ባለቤት ብዙ የስፓኝ ዘሮች ወደ አካባቢው እየገቡ ስለሆነ ንብረቱን በቅናሽ ዋጋ እንዲሸጠው ሲያግባባው ነው። የዚህ ዓይነት አሠራር ህገ ወጥ ነው። ኤጀንቱ በአጠቃላይ ለስፓንሽ ተወላጆችን ልዩ ግምት በመስጠት የንብረቱን ባለቤት የእነሱ ወደ አካባቢው መግባት የንብረቱን ዋጋ ሊያስቀንስበት ስለሚችል ንብረቱን እንዲሸጥ ባለንብረቱን ሲገፋፋው ነው።

**ስላይድ 20**

ሌላው የቤት አድልዎ ገዥውን ማሳሳት ነው። ይህ በጣም የተለመደ ሲሆን፣ የሚደረገው ኤጀንቱ በጣም በተራቀቀ መንገድ ለገዥው የሚሰራ አያስመስለ በተዘዋዋሪ መንገድ አድልዎ ሲያደርግ ነው። ለምሳሌ፦ ኤጀንቱ ልጅ ያላቸውን ቤት ገዥዎች መናፈሻና የልጆች መጫዎቻ ስለሚኖራቸው ከከተማው ወጣ ያሉ ቤቶች እንደሚሻላቸው ሲያግባባቸው ነው። ንብረት ገዥዎቹ መግዛት የሚፈልጉት ከተማው ውስጥ የተወሰነ አካባቢ ሲሆን፣ ኤጀንቱ እነሱ የሚፈልጉትን ሳይሆን ሌላ አካባቢ እንዲገዙ ይገፋፋቸዋል። ላይላዩን ሲያዩት አድሎ ላይመስል ይችላል። ይሁን አንጂ አድልዎ ነው። እነኝህ ቤት ገዥዎች የመረጡት አካባቢ መኖር መቻል አለባቸው።

**ስላይድ 21**

ስለቤት አድልዎ ስናስብ ሰዎች ስለቤቶች መኖር አንዴት አንደሰሙ ማወቅ ጠቃሚ ነው። ድንጋጌው ማንኛውም ማስታወቂያ፣ የጽሁፍ መግለጫ ወይም እትም ምርጫን ወይም እገዳን መጨመርን ይከለክላል። ይህም የተፃፋና በቃል የሚሰጡ ማስታወቂያዎችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ብሮሹሮችን፣ ኮንትራቶችን፣ ምልክቶችን፣ ሰሌዳዎችን፣ ፖስተሮችንና የማስታወቂያ ቦርዶችን ይጨምራል።

ለማንም ሰው ቤት ግዢን በተመለከተ ምርጫ ወይም እገዳ ማድረግ የተከለከለ ነው። ለምሳሌ፣ በጋዜጣ ላይ “የተሟላ 3 መኝታ ቤት ያለው አፓርትመንት፣ ልጆች አይፈቀድም ” ብሎ ማሳተም የተከለከለ ነው። ይህ ድንጋጌውን መጣስ ነው።

**ስላይድ 22**

የፍትህ ቤቶች ድንጋጌ፣ ቤት አከራዮች ምን ማድረግ እንደሌለባቸው ብቻ ሳይሆን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ይገልፃል፦ ይኸውም ተገቢ መኖሪያ ወይም ተገቢ ማሻሻል ማድረግን ይጨምራል።

ተገቢ መኖሪያ የሚገልፀው የአካል ጉዳት ላለባቸው ወይም የአካል ጉዳት ካለባቸው ሰዎች ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ነው። ኗሪዎች ወይም ተከራዮች እንደማንኛውም የአካል ጉዳት የሌለው ሰው ተደስተው ለመኖር ተገቢ መኖርያ የማግኘት ዕድል መስጠት አለባቸው። ለምሳሌ፦ አንድ ተከራይ በአካል ጉዳት ምክንያት ለረጅም መንገድ መሄድ ስለማይችል የአካለ ስንኩል መኪና ማቆምያ ቦታ ቢጠይቅ ተገቢ ነው። በሌላው በኩል አንድ ተከራይ ረጅም መንገድ መሄድ ስለማይችል አከራዩ የየቀኑን ጋዜጣ እንዲያመጣለት ቢጠይቅ አከራዩ ለሁሉም ተከራዮች የሚያደርገው ካልሆነ በስተቀር የአከራዩን መሰረታዊ አሰራር ይለውጣል። ይህ እንደ ተገቢ የመኖርያ ሁኔታ አይቆጠርም።

**ስላይድ 23**

ተከራይ የተሽከርካሪ ወንበር ማስገቢያ ከፈለገ የማሻሻያ ወጭውን ይከፍላል። ሆኖም፣ አከራዩ ከፌደራል መንግሥት ገንዘብ የሚያገኝ ከሆነ አከራይ ወጭውን ይሸፍናል።

**ስላይድ 24**

ስለ አንዳንድ የቤት ችግር የቃል ወይም የጽሁፍ ጥያቄ ለአከራይ ማቅረብ የተከራይ ኃላፊነት ነው። አከራይ ተከራይ ችግር አለው ብሎ መገመት የለበትም።

**ስላይድ 25**

ከመጋቢት 13 ቀን 1991 ዓ.ም. በኋላ የተሠሩ አፓርትመንት መኖሪያዎች ወይም ቤቶች ቢያንስ በሰባት (7) ቴክኒካል የመግቢያ መልክ መሠራት አለባቸው።

1. በቀላል መግባት የሚቻልበት መተላለፊያ
2. የጋራ መግቢያና የሕዝብ ማረፊያ ቦታዎች
3. የሚሠሩ በሮች
4. በዩኒቱ መተላለፊያዎች
5. በቀላል መድረስ የሚቻሉ የመብራት ማጥፊያና ማብሪያዎች፣ የኤሌክትሪክ መሰኪያዎችና የአካባቢ መቆጣጣሪያዎች
6. በመታጠቢያ ቤት ውስጥ ጠንካራ ግርግዳዎች
7. በጥቅም ላይ የሚውሉ ወጥቤትና መታጠቢያ ቤቶች

**ስላይድ 26**

በፌደራልና በዲ.ሲ. ፍትህ የቤቶች ድንጋጌ የተሸፈኑ የንብረት ዓይነቶች ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው። እንደምትመለከቱት ለቤት የተከለለ ባዶ መሬት እንኳን በድንጋጌው ሥር ይካተታል።

**ስላይድ 27**

አሁን በፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ሥር ስላሉ የንብረት ዓይነቶች እንነጋገር። የሚቀጥሉት አራት የንብረት ዓይነቶች በፍትህ የቤቶች ድንጋጌ ሥር አይካተቱም። በነዚህ ንብረቶች ላይ አንድ ሰው አቤቱታ ቢያቀርብ በሥልጣኑ ሥር ስለማይካተቱ ሊሻሩ ይችላሉ።

- የትናንሽ ንብረት ባለቤቶች
- የኃይማኖት ድርጅቶች
- የአዛውንቶች ቤቶች
- የደባል ሁኔታዎች

ምንም እንኳን በፍትህ የቤቶች ድንጋጌ መሰረት የትናንሽ ንብረት ባለቤት ላለማከራየት ነፃ ቢሆንም፣ የአድልዎ መግለጫ ለማውጣት ወይም ለማተም ተጠያቂ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ  የንብረት ባለቤት - "ሁለት መኝታ ቤት ያለው፣ ለአዋቂዎች ብቻ፤ ልጆች  አይፈቀድም"  ብሎ ማስታወቂያ ቢያወጣ- ባለንብረቱ ምርጫ ወይም ገድብ በማሳየቱ በፌደራል የቤቶች ፍትህ ድንጋጌ አንቀፅ 804 መሠረት አድሎአዊ ማስታወቂያ አድርጓል በማለት ክስ ሊቀርብበት ይችላል።

አሁን ሰለ እያንዳንዱን ነፃ ሊሆን የሚቻልበትን እንመለከታለን....

**ስላይድ  28**

...የትናንሽ ንብረት ባለቤቶች ነፃ ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉት ከተሟሉ ነው፣

- ከሶስት የአንድ ቤተሰብ ቤቶች በላይ ከሌላቸው;
- የደላላ ወይም የሽያጭ ወኪል አገልግሎት ካልተጠቀሙ፣ እና
- ህንፃው ከአራት ወይም በታች ዩኒቶች ካሉት እና ባለቤቱ በአንደኛው ዩኒት ውስጥ ከኖረ።

እንደተነጋገርነው፣ አድልው ያለው ማስታወቂያ ከማውጣት ነፃ አይደሉም።

**ስላይድ 29**

የኃይማኖት ድርጅቶች ለንግድ የማይጠቀሙበትን ንብረት ለማህበርተኞቻቸው ወይም ለክለብ ዓባሎቻቸው ቅድሚያ መስጠት ይችላሉ።  ቡድኖችና ክለቦች ግን ዓባልነትን በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ሊከለክሉ አይችሉም።

**ስላይድ 30**

የአዛውንቶች መኖሪያ ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሟሉ ከቤተሰብ ሁኔታ ጥበቃ ነፃ ነው፣

- በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሁሉ ዕድሜያቸው 62 ዓመት ወይም በላይ መሆን፣ ወይም
- ቢያንስ 80 ከመቶ የሆኑት ዩኒቶች ቢያንስ አንድ ሰው 55 ዓመት ወይም በላይ የሆነ መኖር አለበት

አንደገና፣ ይህ ነፃ ያሚያደርጋቸው ከቤተሰብ ሁኔታ ጥበቃ ብቻ ነው።

**ስላይድ  31**

አንድ ሰው ደባል ማስገባት ሲፈልግ የፆታ ምርጫ ለማድረግ ወይም ለመወሰን ነፃ ነው። ይህም በሥራ  ላይ የሚውለው አብረው በመኖር ሽንትቤትና መታጠቢያ ቤት በጋራ ሲጠቀሙ ብቻ ነው።

**ስላይድ 32**

መደምደሚያ - በዲ.ሲ. የቤቶችና የከተማ ልማት መሥሪያ ቤት (HUD) ስለ ፍትህ ቤቶች የዛሬ ዓመት የተላለፈ አንድ አዲስ መረጃ አካፍላችኋለሁ: - የHUD የፆታ ዝንባሌ ሕግ.

የቤቶችና የከተማ ልማት መሥሪያ ቤት (HUD) የፆታ ዝንባሌ ሕግ በሥራ ላይ የዋለው እ.አ.አ. በመጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ.ም. ነው።. ይህ ሕግ የፆታ ዝንባሌ ወይም የፆታ ማንነት ሳይለይ ሁሉም ሰው በመኖሪያ ቤቶችና የከተማ ልማት መሥሪያ ቤት ፕሮግራሞች በእኩልነት እንዲካፈል ያደርጋል። አንድ ሰው በፌደራል ገንዘብ ለተደገፈ ፕሮግራም ሲያመለክት ለፕሮግራሙ ብቁነቱን ለማረጋገጥ ኤጀንቱ የፆታ ዝንባሌ ወይም የፆታ ማንነት መጠየቅ የለበትም።

**ስላይድ 33**

በሕጉ መሠረት ከማንኛውም ክፍል ቢሆኑ በብቁነታችው መሠረት ሁሉም በእኩልነት መስተናገድ አለባቸው።

**ስላይድ 34**

ጥያቄ ካለዎት የዲ.ሲ. ሰብዓዊ መብቶች ቢሮን በ(202) 727 4559 ይደውሉ ወይም በድህረ ገጽ ohr.dc.gov ተመልከቱ። ስለአዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።